## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## ADDIS ABABA UNIVERSITY

# የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የሥነ ምግባርና የዲሲፕሊን ውስጠ ደንብ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

2017 ዓ.ም

# መግቢያ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ዓለም የደረሰበትን ጥበብ በመጠቀም የማኅበረሰቡን ኑሮ ማሻሻል እንዲቻል በዕውቀትና በክህሎት እንዲሁም በመልካም ሥነ ምግባር የዳበረ ትውልድ ለማፍራት የራሱን ጥረት ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

የራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ አዋጁ የተማሪ ቅበላ፤ የዲስፕሊን እርምጃ እና ምርቃትን የሚመለከቱ ጉዳዮች በሴኔት ሕግ እንዲወስን ለዩኒቨርሲቲው ሴኔት ኃላፊነት የተሰጠው በመሆኑና ሴኔቱም በሴኔት ሕጉ ውስጥ ለተመለከቱ የተማሪ ጥፋቶች የቅጣቱ ዓይነትና መጠን በተማሪዎች ጉዳይ ዲን ተዘርዝሮ እንዲወሰን ሥልጣን የተሰጠ በመሆኑ፤

ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲ ቆይታቸው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን ህግ፣ የአካባቢውን ማኅበረሰብ እሴቶች፣ እና የሌሎችን መብቶች እንዲያውቁና እንዲያከብሩ ለማስቻል የራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲን አዋጅ ቁጥር 1294/2015 አንቀጽ 18(4) እና የሴኔት ሕጉን አንቀጽ 148(3)(1) መሠረት በማድረግ ዩኒቨርሲቲው ሴኔት ይህንን የተማሪዎች ሥነ ምግባርና የዲሲፕሊን ውስጠ ደንብ አውጥቷል፡፡

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
Federal Democratic Republic of Ethiopia Addis Ababa University

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ ውስጠ ደንብ "የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የሥነ ምግባርና የዲሲፕሊን ውስጠ ደንብ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

2.1 "ተማሪ" ማለት በዩኒቨርሲቲው ሬጅስትራር ተመዝግቦ በመደበኛ፣ በማታ፣ በክረምት፣ በርቀት፣ በኦንላይን ወይም በሌላ መንገድ በመጀመሪያ ዲግሪ ወይም በድህረ ምረቃ ወይም በማንኛውም ፕሮግራም በመማር ላይ ያለ ሰው ነው፡፡

2.2 "ዩኒቨርሲቲ" ማለት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን ወይም በውስጡ የሚገኙ ሁሉንም ኮሌጆች፣ የምርምር ተቋማት፣ የሥራና የትምህርት ክፍሎችና ግቢዎች ነው፡፡

2.3 "ሴኔት" ማለት በራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ አዋጅ ቁጥር 1294/2015 እና መቋቋሚያ ደንብ 537/2016 መሰረት የተቋቋመና በዩኒቨርሲቲው ውስጥ በአካዳሚክ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ሰጭ አካል ነው፡፡

2.4 "ሥነ ምግባር" ማለት ማንኛውም ዓይነት በግለሰብም ሆነ በተቋሙ ላይ አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ተጽዕኖ ሊያሳርፍ የሚችል ባሕርይ ሆኖ በድርጊት ሊገለጽ የሚችል ነው፡፡

2.5 "የተማሪዎች ዲሲፕሊን ኮሚቴ" ማለት የተማሪዎች ሥነ ሥርዓት ጥሰትን መርምሮ የውሳኔ ሀሳብ እንዲሰጥ በዚህ ውስጠ ደንብ መሰረት የሚቋቋም ጊዜያዊ ወይም ቋሚ ኮሚቴ ነው፡፡

2.6 "አዋጅ" ማለት የራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ አዋጅ ቁጥር 1294/2015 ነው፡፡

2.7 "ፕሬዚዳንት" ማለት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንት ነው፡፡

2.8 "የተማሪዎች ዲን" ማለት በዩኒቨርሲቲው የተማሪዎችን ጉዳይ በበላይነት እንዲመራ ሥልጣን የተሰጠው ግለሰብ ወይም ተወካይ ነው፡፡ ለተማሪዎች መሰረታዊ አገልግሎቶችን የሚሰጥ ወይም እንዲሰጥ የሚያደርግ፣ የሚያስተባብርና የሚያስተዳድር አካል ነው፡፡

2.9 "ዕጩ ምሩቅ" ማለት የመጨረሻውን መመረቂያ የትምህርት ዓመት ፈተና ተፈትኖ ለመመረቅ የተዘጋጀ ተማሪ ነው፡፡



በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
Federal Democratic Republic of Ethiopia Addis Ababa University

2.10 "የተማሪዎች ማኅበር" ማለት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከሚገኙት ኮሌጆች፣ ኢንስቲቲዩቶች እና ትምህርት ቤቶች የሚገኙ የተወከሉ ተወካዮች እና በልዩ ውክልና ከሚወከሉ የአካል ጉዳተኛ ማህበር እና የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሴት ተማሪዎች ማህበር ስብስብ ነው፡፡

2.11 "ሴኩላሪቲ" ማለት አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከሃይማኖት፣ ከብሔር፣ ከዘር እና ከፖለቲካ ተጽዕኖ በፀዳ መንገድ ተልእኮውን፣ ፖሊሲዎቹን፣ ስትራቴጂዎችን፣ አሠራሮችንና ዕቅዶችን መፈጸም እና ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲ ቆይታቸው በዚሁ መርህ መሰረት መተዳደር ሲችሉ ነው፡፡

3. **የተፈጻሚነት ወሰን**

3.1 ይህ ውስጠ ደንብ በዩኒቨርሲቲው በተማሪነት በተመዘገበ ማንኛውም ሰው ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡ ሆኖም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪ ሆኖ በተመዘገበ መምህር ወይም ሠራተኛ የሚፈጸም ጥፋት በሌላ ሁኔታ በዲስፕሊን የሚያስጠይቅ ከሆነ ይህ ውስጠ ደንብ በድጋሚ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

3.2 ውስጠ ደንቡ ተፈጻሚ የሚሆነው ተማሪው በተማሪነት ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ ተመርቆ ወይም በሌላ ምክንያት ተማሪነቱ እስኪያበቃ ድረስ ባለው የጊዜ ወሰን ነው፡፡

3.3 አንድ ተማሪ በዩኒቨርሲቲው ግቢዎች ውስጥም ሆነ ውጪ ከትምህርት ወይም ተማሪነት ጋር በተያያዘ በሚፈጽማቸው ዩኒቨርሲቲውን ወይም የዩኒቨርሲቲውን ማኅበረሰብ በሚጎዱ የደንብ ጥሰቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

3.4 ይህ ውስጠ ደንብ በጊዜያዊነት ለትምህርት፣ ለልምምድ ወይም በሌላ ሁኔታ በዩኒቨርሲቲው በሚገኙ የሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች ተማሪዎች፣ ተለማማጆች ወይም የምርምር ሥራ በሚሠሩ ተማሪዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

4. **ዓላማ**

የዚህ ውስጠ ደንብ ዓላማ ዩኒቨርሲቲው እና የዩኒቨርሲቲው ማኅበረሰብ ሥራ በአግባቡ እንዲካሄድ ለማስቻል እንዲሁም የሥነ ሥርዓት ጥሰት ለሚፈጽሙ ተማሪዎች የባህርይ ማስተካከያና ማረሚያ ትምህርት መስጠት ነው፡፡

5. **የጾታ አገላለጽ**

የቃላት አገባቡ የተለየ ትርጉም የሚያሰጥ ካልሆነ በቀር በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴት ጾታንም ያካትታል፡፡



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Addis Ababa University

## ክፍል ሁለት
## በዩኒቨርሲቲ ቅጥር ግቢ ውስጥ የአለባብስና አምልኮ ስርዓት

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን ራስ ገዝ ሆኖ ለማቋቋም በወጣው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 537/2016 እና በራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ አዋጅ ቁጥር 1294/2015 መሰረት ከሚጠበቁበት ጉዳዮች አንዱ፤ የዩኒቨርሲቲውን ማኅበረሰብ በሴኩላሪቲና በመልካም እሴቶች መርኅ በመምራት ከሃይማኖታዊ፣ ፖለቲካዊና ባህላዊ ልዩነቶች በጸዳና ብዝሃነትን ተቀብሎ በማበረታታት ልዩነቶችን በመቻቻል እና በመከባበር መርኅ ላይ ተመስርቶ ሰላማዊ የመማር ማስተማር ሂደትን ማስቀጠል ነው። ስለዚህ የአለባበስና የአምልኮ ሥርዓት ላይ የጋራ ግንዛቤ እንዲኖር በዚህ ውስጠ ደንብ ውስጥ ማካተት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

### 6. አለባበስ

6.1 በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ስር የሚገኙ ግቢዎች የተለያዩ እምነቶች ተከታይ የሆኑ ተማሪዎችን ስለሚያስተናግዱ ከሃይማኖትና ከበዓላት ጋር የተያያዙ የአለባበስ ስርዓቶች የማንነትና የእምነት መገለጫዎች በመሆናቸው ሊከበሩ ይገባቸዋል።

6.2 በመመገቢያ ቤቶች፣ በመማሪያ ክፍሎችና አብያተ መጻሕፍት ውስጥ የቤት ውስጥ መገልገያ ብቻ የሆኑ ነጠላ ጫማ፣ የሌሊት ልብስ፣ ወይም ፒጃማ እና ሌሎች ከቤት ውጪ ላሉ አካባቢዎች ተገቢ ያልሆኑትን አልባሳት ለብሶ መምጣት የተከለከለ ነው።

6.3 የተተለተለ፣ የተቀደደ፣ ገላን የሚያሳይ ልብስ መልበስና፣ ተረከዘ ረጃጅምና ድምጽ የሚያወጡ ጫማዎችን መጫማት፣ ጸጉርን ማንጨብረር፣ ቅርጽ ያለውና የተለየ ቀለም መቀባት የተከለከሉ ናቸው።

6.4 እንደ ሁኔታው በመማሪያ ክፍሎችና የተግባር ትምህርትና ልምምድ በሚሰጥባቸው ቦታዎች ሙያው ወይም ስልጠናው የሚፈልገው ዓይነት የአለባበስ ሥርዓት መከበር ይኖርበታል።

6.5 የሌላውን እምነት፣ ታሪክ፣ ክብርና ሞገስ የሚያጣጥል ወይም የሚያናንቅ ምስልና ጽሑፍ የተጻፈበትን አልባሳት መልበስ የተከለከለ ነው።

6.6 በአንቀጽ 6.1. ላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በዩንቨርሲቲው ከሚከናወኑ የመማር ማስተማር ተግባራትና ከሚሰጡ አገልግሎቶች ጋር በተያያዘ ማንነትን ለመለየት ሲባል በዩንቨርሲቲው ቅጥር ግቢ ውስጥ ፊትን ሙሉ በሙሉ የሚሸፍኑ አለባበሶችን መልበስ የተከለከለ ነው።

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ Federal Democratic Republic of Ethiopia Addis Ababa University

6.7 ከተማሪነት በተጨማሪ በሚከተሉት እምነት ውስጥ/ዘንድ ባላቸው ሃይማኖታዊ ሚና የተለየ የእምነት አለባበስ እንዲኖራቸው ስለማስፈለጉ አሳማኝ ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ ሰዎች በልዩ ሁኔታ ሃይማኖቱ የሚፈቅደውን አለባበስ መልበስ ይችላሉ።

6.8 አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የማንኛውንም ብሔር፣ ዘር ወይም ፖለቲካዊ አቋም ማራመጃ መሆን የሌለበት በመሆኑ የተማሪዎች አለባበስም ነጻ የሆነና የፖለቲካ መልእክት የሚያስተላልፍ መሆን የለበትም።

## 7. አምልኮ

7.1 ማንኛውም ተማሪ በግሉ የፈለገውን ሃይማኖት የመከተል መብት አለው። በማንኛውም ቦታ በግሉ የሌላውን ሰው እምነት፣ ስሜት፣ ፀጥታ ወዘተ... በማያውክ ሁኔታ የግሉን ፀሎት ማድረግ ይችላል። ይህ ግን በመጮህ ወይም የሌላውን ሰው ነፃነትና ፀጥታ በሚነካ መልኩ መሆን የለበትም።

7.2 በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የተለየ የአምልኮ ቦታ መጠየቅ፣ መስራትም ሆነ የተወሰነ ሕንፃ ወይም መኝታ ቤት ለአምልኮ ወይም ለሃይማኖታዊ፣ እንዲሁም ለፖለቲካዊ ጉዳይ ወይም ለስብሰባ መጠቀምም ሆነ በቡድን ተሰባስቦ ሃይማኖታዊ ሥርዓት ማካሄድ የተከለከለ ነው።

7.3 በማናቸውም መልኩ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቅጥር ግቢ የማናቸውንም ሃይማኖት በቡድን ሰበካ ማካሄድ፣ በቡድን መዘመር፣ በቡድን መፀለይ፣ በቡድን መስገድ አይቻልም።

7.4 የተለያዩ የሃይማኖት መቀስቀሻ የሆኑና ከሃይማኖት ጋር ተያያዥነት ያላቸው የሕትመትና የኤሌክትሮኒክስ ውጤቶችን በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ግቢ ማሰራጨትና በመቀስቀሻነት መጠቀም አይፈቀድም።



በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
Federal Democratic Republic of Ethiopia Addis Ababa University

## ክፍል ሶስት
## መብቶችና ግዴታዎች

በሴኔቱ ሕግ የተዘረዘሩት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የተማሪዎች መብቶችና ግዴታዎች ከዚህ በታች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### 8. የተማሪዎች መብቶች

8.1 በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ሴኔት ባወጣው የትምህርት የጊዜ ሠሌዳ መሠረት በነጻነት የመማር፣ የመጠየቅ፣ የመመራመር፣ የመረዳት፣ የማወቅ፣ ሳይንሳዊና ጥበባዊ ክህሎትን የማሳደግ፣ ልቀ መገኘት፣

8.2 በሃይማኖት፣ ብሔር፣ ዘር፣ ጾታ፣ ፖለቲካዊ አመለካከትና በመሳሰሉት ምክንያቶች አድልኦ እንዳይደርስባቸው ሕጋዊ ከለላ የማግኘት፣

8.3 በዩኒቨርሲቲው የሚሰጡ አገልግሎቶችን ሃይማኖትን፣ ጾታን፣ ብሔርን፣ ዘር ወይም ፖለቲካዊ አመለካከትን መሰረት ሳያደርግ እኩል የማግኘት፣

8.4 በመማሪያ ክፍሎች፣ በዩኒቨርሲቲው ግቢዎችና በኅብረተሰቡ ውስጥ ለመማር አመቺ ሁኔታን የማግኘትና የመጠቀም፤

8.5 በዩኒቨርሲቲው ግቢዎች ውስጥ ሕገ መንግስታዊና ሰብዓዊ መብታቸውና ደህንነታቸው ተጠብቆ የመኖር፣

8.6 በዩኒቨርሲቲ ጉዳዮች ላይ በሕጋዊና በሰላማዊ አግባብ አቋማቸውን በነጻነት የማራመድ፤

8.7 በማንኛውም የመምህርና የተማሪ ግንኙነት የፍትህና ፍትሃዊነት ተጠቃሚ የመሆንና ለመማር የሚያነሳሳ መልካም ተቋማዊ ድባብን የማግኘት፣

8.8 ስለአካዳሚያዊ ብቃታቸው በራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ አዋጅ በተደነገጉ መርሆዎችና በዩኒቨርሲቲው አካዳሚክ መመዘኛዎች መሰረት የመመዘን፣ ኢፍትኃዊ ምዘና ተፈጽሟል ተብሎ ሲታመን ቅሬታን በዩኒቨርሲቲው ሥርዓት መሠረት በሰላማዊና ሕጋዊ መንገድ የማቅረብና ፍትሕን የማግኘት፤

8.9 ግልጽነት ባለው ሥርዓት መሠረት የመምህራንንና ሌሎች አካዳሚክ ሰራተኞችን የሥራ አፈጻጸም ግምገማ መሙላትና በአፈጻጸም ግምገማው ላይ በመሳተፍ አስተያየት የመስጠት፣

8.10 በትምህርት ማህደራቸው ዉስጥ የሚቀመጡ መረጃዎች በምስጢር ስለሚጠበቁበትና ለሌላ ወገን ስለሚገለጹበት ሁኔታ የሚወስን አስተማማኝ ስርዓት ተጠቃሚ የመሆን፣

8.11 የተማሪዎች የጋራ ጥቅሞችን በሕጋዊ መንገድ እንዲጠበቁ ለማስቻል አግባብነት ባላቸው ሕጎች በተቋቋመና የዩኒቨርሲቲውን ተማሪዎች በአባልነት በሚያቅፈው የዩኒቨርሲቲው የተማሪዎች ኅብረት አባል የመሆን፣



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Addis Ababa University

8.12 በዩኒቨርሲቲው ደንብና ሥርዓት መሠረት በግልም ሆነ በኅብረታቸው አማካይነት ዩኒቨርሲቲው በሚያቀርባቸው መገልገያዎች የመጠቀም፣

8.13 በራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ አዋጅ ድንጋጌዎችና የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ቦርድ በሚያወጣቸው መመሪያዎች መሠረት በኅብረታቸው ወይም በተወካዮቻቸው አማካኝነት በተለያዩ የዩኒቨርሲቲው አካዳሚያዊና አስተዳደራዊ ስብሰባዎች ላይ የመሳተፍ፣

8.14 ከትምህርት ጋር አግባብነት ያላቸውን ሀሳቦች የማቅረብ፣ የመከራከርና የመወያየት፣

8.15 ከዩኒቨርሲቲው ማኅበረሰብ ጋር ለሚፈጠሩ ማንኛውም የዲሲፕሊን ግድፈቶች ወይም አለመግባባቶች በተገቢው አካል የመዳኘት እና አግባብነት ያለው ፍትሕ የማግኘት፣

8.16 በዩኒቨርሲቲው ውስጥ በሚቋቋሙ በተማሪዎች ኅብረት፣ ካውንስል፣ የተማሪዎች ክበባትና ሌሎች አግባብነት ባላቸው አደረጃጀቶች (ለምሳሌ የመኝታ ቤት፣ የመኖሪያ ሕንፃ፣ የዲስኘሊን፣ የመዝናኛ፣ የምግብ ቤት፣ የፀረ-ኤድስ፣ የጤና፣ የአካባቢ፣ የስፖርትና የመዝናኛ ወዘተ) ውስጥ ሃይማኖትን፣ ብሔርን ወይም ዘርን እና ፖለቲካዊ መሰረት ሳያደርግ በአመራርነትም ሆነ በአባልነት የመሳተፍ፣

8.17 በዩኒቨርሲቲው የሴኔት ሕግ የተካተቱትን መብቶች በአግባቡ የመጠቀም፣

8.18 በጥፋተኝነት በሚከሰሱበት ጊዜ የተከሰሱበትን ወይም የተጠረጠሩበትን ጉዳይ በተመለከተ የበኩላቸውን ማስረጃና ክርክር የማቅረብ፣

8.19 በአካዳሚክና በአስተዳደራዊ ጉዳዩች ዙሪያ በሰላማዊ ሁኔታ የመወያየትና ሐሳብ የመስጠት ብሎም ፓናል ውይይት የማዘጋጀት፣

8.20 በዩኒቨርሲቲው የሴኔት ሕግ መሰረት በማንኛውም የመማር ማስተማር አገልግሎት በሚሰጥበት መስክ በብሄር፣ በጾታ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ ወይም በሌላ ወገንተኝነት ምክንያት አድልኦ የማይደረግበት መሆኑን መረዳት፤ ከተደረገበትም ለሚመለከተው የአመራር አካል ቅሬታውን የማቅረብና ምላሽ የማግኘት፤

8.21 ቤተ ሙከራዎችና ወርክሾፖች እንዲሁም ሌሎች ትምህርቱን ሊያግዙ የሚችሉ የዩኒቨርሲቲውን ወይም የሌሎች ተቋማትን በሚመለከተው አካል ክትትል የመጠቀም መብቶች አለው፡፡

**9. የተማሪዎች አጠቃላይ ግዴታዎች፤**

9.1 የከፍተኛ ትምህርት ዓላማዎችንና የዩኒቨርሲቲውን መሪ እሴቶች የማወቅና የማራመድ፤

9.2 አግባብነት ያላቸውን የሀገሪቱን ህጎች፣ የዩኒቨርሲቲውን የተማሪዎች ዲሲፕሊን ውስጠ ደንብ፣ የተቋሙን የሴኔት ሕግ እንደዚሁም ሌሎች ተፈፃሚነት ያላቸውን ህጎች የማወቅ፣ የማክበርና የማስከበር፣



በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Addis Ababa University

9.3 እያንዳንዱ ተማሪ በተማሪነት ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ ዲፕሎማውን እስኪቀበል ወይም በሌሎች ምክንያቶች ዩኒቨርሲቲውን እስከሚለቅበት ዕለት ድረስ ለሚያሳየው ባሕርይ ኃላፊነት የመውሰድ፣

9.4 ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲው ውስጥ የሚኖራቸው ባህርይ በዩኒቨርሲቲው የተገኙበትን ዓላማ የሚያሳካ በተለይም ለመማር ማስተማር፣ ለምርምር እና ለማኅበረሰብ አገልግሎት ያላቸውን ሚና ለመወጣት በሚያስችላቸው ሁኔታ ላይ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣

9.5 ተማሪዎች ከዩኒቨርሲቲው ግቢ ውጭ ከመማር፣ ከምርምር ወይም ከማኅበረሰብ አገልግሎት ጋር ባልተያያዘ ነገር ግን ተማሪነታቸው በሚለይበት ሁኔታ የሚያሳዩት ባሕርይ የዩኒቨርሲቲውን መልካም ዝና የማያጎድፍ መሆኑን የማረጋገጥ፣

9.6 የተማሪዎች የግልም ሆነ የጋራ ጥቅም አደጋ ላይ በሚወድቅበት ጊዜ ፍጹም ሰላማዊና ሕጋዊ በሆነ መንገድ ቅሬታን በማሰማት በጋራ መፍትሄ የመሻት፣

9.7 የዩኒቨርሲቲውን የጋራም ይሁን የግል መገልገያ ንብረት በጥንቃቄ የመያዝና የመጠቀም፣ ሆን ተብሎ ወይም በቸልተኝነት ምክንያት በዩኒቨርሲቲው ንብረት ላይ ለሚደርሰው አደጋና ለሚከሰተው ማንኛውም ጉዳት በጋራም ሆነ በግል ተጠያቂ የመሆን፣ እንደዚሁም የደረሰውን ጉዳት የመተካት፣ ጥፋት ያደረሰውን አካል የማጋለጥ፤

9.8 ዩኒቨርሲቲው ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች መከፈል የሚገባውን ክፍያ የመፈፀም፤

9.9 ሁልጊዜ የተማሪ መታወቂያ ካርድ መያዝና ለሌላ አካል አሳልፎ አለመስጠት፣ በሚመለከተው አካል ሲጠየቁም የማሳየት፣

9.10 በዩኒቨርሲቲው የተደነገገውን የምሽት ወደ ግቢ መግቢያና መውጫ ሰዓት የማክበር፤

9.11 ማንኛውንም መምህር፣ የአስተዳደር ሰራተኛ እንዲሁም የመማር ማስተማርንና የአስተዳደር ሂደቱን የመምራትና የመቆጣጠር ኃላፊነት ያለውን አካል የማክበር፣

9.12 ወረፋ ባለበት ቦታ ሁሉ ወረፋን ጠብቆ የመገልገል፣

9.13 በማንኛውም ጊዜ ግቢውን ሲለቁ የተረከቡትን ንብረት በአግባቡ ቆጥሮ ማስረከብ፣ ክሊራንስ በማግኘት ግቢውን በወቅቱ መልቀቅ፣

9.14 ሱስ ከሚያስይዙ (ጫት፣ ሲጋራ፣ አልኮል፣ ሺሻና የመሳሰሉት) ጎጂ ልማዶች ራስን የመጠበቅ፣

9.15 ከዩኒቨርሲቲው ግቢ ውጪ ካለው ማኅበረሰብ ጋር በሚኖረው ግንኙነት በመልካም ስነ-ምግባር አርአያ የመሆን፣

9.16 የሌላውን ባህል፣ ቋንቋ፣ ሃይማኖት፣ ወዘተ የማክበርና የመጠበቅ፣

9.17 ከማንኛውም ሕገወጥና ከሥነ ምግባር ውጭ ከሆኑ ተግባራት የመቆጠብ፣ ለምሳሌ ከስርቆት፣ አላግባብ በመጮህ ሌላውን ከማወክ፤ ለሕገ ወጥ ተግባር ሌሎችን ከማነሳሳት፤



Federal Democratic Republic of Ethiopia Addis Ababa University

9.18 ማንኛውም ተማሪ ከመኝታ ክፍሉ ውጭ ሄዶ ያለመተኛት፣ ሌላ ተማሪም አስደርቦ አለመገኘት፣ ያለፈቃድ የመኝታ ክፍል አለመቀያየር

9.19 በመኝታ ቤት ምንም ዓይነት ተቀጣጣይ ነገሮችን ያለመያዝ፣ ምግብ ማብሰልና ካውያ አለመጠቀም እና ምንም አይነት ሰው ሊጎዳ የሚችል መሳሪያ ይዞ አለመገኘት፣

9.20 በተማሪዎች መካከል በማናቸውም ምክንያት ጸብ ሲነሳ ለሚመለከተው አካል ወዲያውኑ ማሳወቅ፤ በተማሪዎች መካከል የሚነሱ ግላዊ ጸቦችን ወደ ብሔርና ሃይማኖት በመለወጥ ግጭት ውስጥ አለመግባት፣

9.21 ከትምህርት ጋር ተያይዘው የሚሰጡ ሥራዎችን በራስ ጥረት መሥራት፣ የሌላ ሰው ሥራ የራስ አስመስሎ አለማቅረብ፣ ለሌላ ሰው ሠርቶ መስጠት ወይም ከሌላ ሰው መውሰድ ወይም መኮረጅ የማይቻልና ዋጋ የሚያስከፍል መሆኑን የመረዳት፤

9.22 ተማሪዎች ለማንኛውም የዩኒቨርሲቲው ማኅበረሰብ አባል ተገቢውን ክብር የመስጠት፣

9.23 ተማሪዎች በቃላት አጠቃቀማቸው፣ በሚያሳዩት ባሕርይና በሚኖራቸው የእርስ በእርስ ግንኙነት የሌሎችን መብትና ስሜት የመጠበቅ፣

9.24 ተማሪዎች ለውሳኔ አሰጣጥ አስፈላጊ የሆኑ ፍሬ ነገሮችን እንዲገልጹ በሚያስፈልግበት ጊዜ እውነትና ሙሉ እውነቱን ብቻ የመናገር ወይም የመግለጽ ግዴታ አለባቸው፡፡

9.25 በአጠቃቀም ጉድለት፣ በቸልተኝነት ወይም ሆነ ተብሎ በዩኒቨርሲቲው ንብረት ላይ የሚደርስን ጉዳት፣ ጉድለት ወይም የዋጋ መቀነስ የመተካት፣

9.26 የደረሰው ጉዳት በዩኒቨርሲቲው ንብረት ላይ ከሆነ በገንዘብ መካስ ያልቻለ ተማሪ ማኅበራዊ አገልግሎት እንዲሰጥ ሊጠይቅና ሊፈቀድለት ይችላል፡፡

9.27 ተማሪዎች በተለይ የኮምፒዩተር እና ኢንተርኔት አጠቃቀም፣ የመኖሪያ እና የምግብ ቤት አካባቢ መመሪያዎችን፣ የቅጂ መብት እና የላይብረሪ አጠቃቀም ፖሊሲዎችን የማክበር፣

9.28 ተማሪዎች የዩኒቨርሲቲውን ንብረት በተገቢው ጥንቃቄ፣ ለሌሎች እድል በመስጠትና በመጋራት የመጠቀም፣

9.29 የተማሪዎች አለባበስ ስነ ምግባርን የማይቃረን፣ መልካም ግንኙነትን የማይረብሽ ተገቢ ስርዓት የተከተለ መሆኑን የማረጋገጥ ግዴታ አለባቸው፡፡

# ክፍል አራት
# በተማሪዎች መኝታና ምግብ ቤት የተከለከሉ ተግባራት

## 10. በተማሪዎች መኝታ ቤት የተከለከሉ

10.1 የዩኒቨርሲቲው ተማሪ ያልሆነ ወይም የተባረረ ተማሪ በመኝታ ቤት ማሳደር ወይም ማኖር፣

10.2 ተደራራቢ አልጋዎችን መገንጠል፣ ፍራሽ መሬት ላይ አውርዶ መተኛት፣

10.3 የኤሌክትሪክ መስመሮችን ጠልፎ ለሌላ አገልግሎት ማዋል፣

10.4 ወደተቃራኒ ጾታ መኝታ ክፍል ውስጥ መግባት ወይም ማስገባት፣

10.5 በህመም ምክንያት ካልተፈቀደ፣ ከዳቦና ከደረቅ ምግቦች በስተቀር የበሰሉ ምግቦችን ወደ መኝታ ክፍል ይዞ መግባት፣

10.6 የመኝታ ቤት ቁልፍ በሚመለከተው አካል ሳይፈቀድ ማስቀረጽ፣

10.7 በአንድ አልጋ ላይ ከአንድ በላይ ሆኖ መቀመጥ ወይም/እና መተኛት፣

10.8 በመስኮት መውጣትና መግባት ፣

10.9 በማንኛውም ጊዜ በመኝታ ክፍል ውስጥና አካባቢ ጫጫታና ረብሻ መፍጠር ወይም የሚረብሽ ድምጽ ማሰማት፣

10.10 የመጸዳጃ ቤቶች፣ የልብስና የእጅ መታጠቢያ ገንዳዎች፣ የፍሳሽ ማስረጊያ ቀዳዳዎችን አላስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን በመክተት እንዲዘጉ ማድረግ፣ መብሳትና መቅደድ፣

10.11 በመኝታ ክፍል ውስጥ አልጋን በመጋረጃ መጋረድ፤

10.12 የሚመለከተውን ክፍል ሳያስፈቅዱ በመኝታ ክፍል ውስጥ እና አካባቢ ስብሰባ ማድረግ፣

10.13 በመኝታ ክፍል ውስጥና አካባቢ በቡድን ሆኖ መፀለይ ወይም መስገድ ፣

10.14 በመኝታ ክፍል ውስጥ ምግብ ማብሰል፣ ሻይና ቡና ማፍላት ፣

10.15 የአገልግሎት ሠራተኞችን ማመናጨቅና መገላመጥ፣ መሳደብ፤ መዝለፍ፤ ስም ማጥፋት፤ ማስፈራራት፣

10.16 የተመደቡበትን የመኝታ ክፍል ያለፈቃድ መቀየር፤ ባልተመደቡበት የመኝታ ክፍል ውስጥ ተዳብሎ መተኛት ወይም አዳብሎ ማስተኛት፣

10.17 በመጸዳጃ ቤቶች፤ በመማሪያ ክፍሎች፣ በግድግዳዎች፣ መዝጊያዎች፣ መስኮቶችና ቁምሳጥኖች ላይ ማንኛውንም አይነት ጽሑፍ መጻፍ፣ ስእል መሳል ወይም መለጠፍ፣ ሚስማር መትከል ወይም መምታት፤

10.18 በየትኛውም ቦታ የእግር ጫማን አጥፎ ግድግዳ ላይ ማሳረፍና ማቆሸሽ፤ ቆሻሻን ወደተገቢው የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ቅርጫት አለመጣል፤



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
Federal Democratic Republic of ... Addis Ababa University

10.19 በግቢ ውስጥ ጫት፣ ሲጋራ፣ አልኮል መጠጦችና አደንዛዥ እፆችን ይዞ መግባት ወይም ሲጠቀሙ መገኘት፣

10.20 በእጅና ፊት መታጠቢያ ገንዳዎች እንዲሁም በመኝታ ክፍል ውስጥና በመተላለፊያዎች (ኮሪደር) ውስጥ ወይም አካባቢ ልብስ ማጠብ፣

**11. በተማሪዎች ምግብ ቤት የተከለከሉ**

11.1 የራስ ባልሆነ መመገቢያ ካርድ መመገብና የራስን መመገቢያ ካርድ ለሌላ አካል አሳልፎ መስጠት፣

11.2 የአንገት ፎጣ፣ ኮፍያ፣ ነጠላ፣ ስሊፐር ጫማ፣ የሌሊት ልብስ፣ ፒጃማ እና ሌሎች ተገቢ ያልሆኑ አልባሳትን ለብሶ ወደምግብ ቤት መምጣት፣

11.3 በምግብ አዳራሽ ውስጥና አካባቢ ከሰራተኞች ወይም ከተማሪዎች ጋር ግጭት መፍጠር፣ ሰልፍ መጣስ፣

11.4 ጥያቄ ወይም ቅሬታ ሲኖር በተወካይ ወይም በራስ ሥርዓትን ጠብቆ ለሚመለከተው አካል ማቅረብ እንጂ ያልተገባ ባሕርይ ማሳየት፣ ሁከት መፍጠር ወይም እንዲነሳ ማድረግ፣

11.5 በምግብ አዳራሽ ውስጥ እጅን መታጠብ፣

11.6 በህመም ምክንያት መንቀሳቀስ ከማይችሉ ተማሪዎች በስተቀር ከዳቦ ውጭ ምግብ ከተማሪዎች ምግብ ቤት ማውጣት፤

11.7 የህክምና ማስረጃ ሳይኖር፣ በተማሪዎች ምግብ ቤት ለተማሪዎቹ በእለቱ ከተዘጋጀው የምግብ አይነት ውጪ አገልግሎት መጠየቅ፣ ይህንንም ተከትሎ አምባጓሮ መፍጠር፣

11.8 ተማሪዎች በጾምና በጸሎት ምክንያት በዕለቱ መጠቀም ያልቻሉትን የምግብ በጀት በማካካሻም ይሁን በጥሬ ገንዘብ መጠየቅም ሆነ ከዳቦ ውጭ ያሉትን ተዳባይ ምግቦች ከመመገቢያ አዳራሽ ይዞ መውጣት፣ ሆኖም እንደ አስፈላጊነቱ ለተማሪዎች የሚዘጋጁ የጾምም ይሁን የፍስክ ምግቦች ሃይማኖትንና ሃይማኖቱ የሚያዘውን የመመገቢያ ሰዓት መሠረት አድርገው ሊዘጋጁ ይችላሉ፡፡

11.9 በምግብ አዳራሽ በመመገቢያ ሰዓት በቡድን መጸለይ አይቻልም፡፡

## ክፍል አምስት
## ጥፋትና የጥፋት ምደባ

### 12. ጥፋት

12.1 ተማሪ ጥፋት ፈጸመ የሚባለው በዩኒቨርሲቲው፣ በሠራተኞችና በተማሪዎች መደበኛ እንቅስቃሴና ሥራ ላይ ተገቢ ያልሆነ ጣልቃ ገብነት፣ መልካም ግንኙነትን የሚያደፈርስ ወይም የዩኒቨርሲቲውን አሠራር ሂደት የሚጎዳ ድርጊት ሲፈጸም ነው፡፡

12.2 ተማሪ ጥፋት ወይም የሥነ ሥርዓት ጥሰት ፈጽሟል የሚባለው፡ -

12.2.1 በዚህ ውስጠ ደንብና በሴኔት ህጉ ጥፋት ተብለው የተመለከቱትን ተግባራት ሲፈጽም፤ወይም

12.2.2 በአገሪቱ ሕግ ጥፋት ወይም የወንጀል ድርጊት ተብለው የተመለከቱትንና ከመማር ማስተማር ወይም ከአግልግሎት ጋር ቀጥታ ግንኙነት ያላቸውን ድርጊቶች ሲፈጽም ነው፡፡

### 13. የጥፋቶች ምደባ

13.1. በተማሪዎች የሚፈጸሙ ጥፋቶች አካዳሚክ፣ ተቋማዊ እና ጾታዊ ተብለው ይመደባሉ፡፡

13.1.1. አካዳሚክ ከመማር ማስተማር ጋር የተያየዙ ጥፋቶች ናቸው፡፡

13.1.2. ጾታዊ የሚባሉት ደግሞ ከጾታ ትንኮሳና ጾታዊ ጥቃት ጋር ዝምድና ያላቸው ጥፋቶች ናቸው፡፡

13.1.3. ተቋማዊ የሚባሉት ከአካዳሚክ እና ጾታዊ ትንኮሳና ጥቃት ውጭ የሆኑ ከአገልግሎት ጋር የተያያዙ ጥፋቶች ናቸው፡፡

13.2. ጥፋቶች እንደክብደታቸው ቀላል፣ መካከለኛ ወይም ከባድ ተብለው ይመደባሉ፡፡

### 14. የወንጀል ድርጊቶች

14.1 በኢትዮጵያ ሕግ የወንጀል ድርጊት ተብለው የተለዩና ከዚህ ውስጠ ደንብ ዓላማ አንጻር ተማሪው የሥነ ምግባር ጥሰት ፈጽሟል የሚያስብሉ ወይም ተማሪውን የዩኒቨርሲቲው ማኅበረሰብ አካል ሆኖ ለመቀጠል ብቁ የማያደርጉት ወይም ከሚማረው ትምህርት ወይም ከተማሪነቱ አንጻር የብቁነት ጥያቄ የሚያስነሱ ተግባራትን ፈጽሞ የተገኘ ተማሪ በወንጀል መጠየቁ እንደተጠበቀ ሆኖ የዲስፕሊን እርምጃ ይወሰድበታል፡፡

14.2 የሚወሰደው የዲስፕሊን እርምጃ የወንጀል ክስ ከመቅረብ አለመቅረቡ ወይም የጥፋኝነት ውሳኔ ከመስጠት አለመሰጠቱ ጋር የሚያያዝ አይደለም፡፡



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
Federal Democratic Republic of Ethiopia Addis Ababa University

## ክፍል ስድስት
## የጥፋቶች ደረጃና ቅጣት

በዚህ ውስጠ ደንብ መሰረት ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ቅጣት የሚያስከትሉ ጥፋቶች ናቸው

**15. የቃል ማስጠንቀቂያ የሚያሰጡ ጥፋቶች ፣**

15.1 በልዩ ሁኔታ የሚፈቀድላቸው ካልሆኑ በስተቀር አገልግሎት መስጫ ቦታዎች ላይ ወረፋን አለመጠበቅ፤

15.2 ከተፈቀዱ ሰሌዳዎች ውጭ ማስታወቂያዎችን መለጠፍ፤

15.3 ዩኒቨርሲቲው ባወጣው አሰራር መሰረት መታወቂያ እንዲያሳይ ተጠይቆ ፈቃደኛ አለመሆን፤

15.4 ወንበሮችንና ጠረጴዛዎችን፣ እንዲሁም ሌሎች መገልገያ ቁሳቁስን ከተመደበላቸው ቦታ ውጭ ማንቀሳቀስ፣ ከተቀመጡበት ክፍል ማውጣት፣

15.5 መመገቢያ እቃዎችን ወደ ቦታቸው አለመመለስ፤

15.6 በመኝታ ቤት ውስጥ ማብሰል፤

15.7 ውሃና ኤሌክትሪክ ያለ አግባብ መጠቀም ወይም ማባከን፤

15.8 አትክልቶችን መርገጥ ወይም መቁረጥ፤

15.9 ፍራሽ ከአልጋ አውርዶ መገኘት፤

15.10 የታጠበ ልብስን ከልብስ ማስጫ ቦታ ውጭ ማስጣት፤

15.11 ከተፈቀደ ቦታ ውጭ ልብስ ማጠብ፤

15.12 በጋራ የመገልገያ አካባቢዎች ከፍተኛ ድምጽ ወይም ጩኸት ማሰማት ወይም ሬዲዮ ወይም ቴፕ በማስጮህ የአካባቢን ፀጥታን ማደፍረስ፤

15.13 ወደ ቅጥር ግቢና መኝታ ህንፃ መግቢያ ተብሎ የተደነገገን የሰዓት ገደብ አለማክበር፤

15.14 በግድግዳዎች ላይ መጻፍ፣ ምስል ወይም ስዕል መለጠፍ፣ መሳል፤

15.15 ከተፈቀደ ቦታ ውጭ በዩኒቨርሲቲው ግቢ ውስጥ ቆሻሻ መጣል፤

15.16 የመኝታ ክፍልን በንጽህና አለመያዝ፤

15.17 ግድግዳ በሚስማር ወይም በመሰል ነገር መብሳት፤

15.18 በምግብ ቤት ውስጥ እጅን መታጠብ፤

15.19 ወደ ምግብ ቤት የአንገት ፎጣ፣ ኮፍያ፣ የቤት ውስጥ መጫሚያ፣ የሌሊት ልብስ ወይም ፒጃማ፣ እና ሌሎች ተገቢ ያልሆኑ አልባሳትን ለብሶ መሄድ



Federal Democratic Re... Addis Ababa University

16. የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ የሚያሰጡ ጥፋቶች

16.1 ከዚህ በላይ በውስጠ ደንብ ቁጥር 15 ከተጠቀሱት መካከል አንደኛው የሥነ ሥርዓት ጥሰት ተፈፅሞ በተወሰደው ቅጣት መሻሻል ሳይታይና ያንኑ ወይም ተመሳሳይ የሥነ ስርዓት ጥሰት መፈጸም፤

16.2 በዩኒቨርሲቲው ንብረት ሳይፈቀድ ወይም አላግባብ መጠቀም፤

16.3 በዩኒቨርሲቲው ውስጥ በተገቢው አካል የተሰጠን ሕጋዊ ትእዛዝ አለማክበር ፤

16.4 በራስ ባልሆነ ካርድ በመመገቢያ አዳራሽ ተገኝቶ መመገብ ወይም ለመግባት ሙከራ ማድረግ፣

16.5 ያልተፈቀደለት ተማሪ በመኖሪያ ቦታ እንዲኖር፣ እንዲዳበል ወይም እንዲያድር ማድረግ፤

16.6 በምግብ አዳራሽ ውስጥ እና አከባቢ ግጭት መፍጠር፣ ወረፋ መጣስ፣

16.7 በምግብ ዙርያ ጥያቄ ወይም ቅሬታ ሲኖር ሥርዓትን ጠብቆ ለሚመለከተው አካል ማቅረብ ሲገባ፣ ያንን ባለማድረግ ያልተገባ ባህርይ ማሳየት፣ ሁከት መፍጠር ወይም ሁከት እንዲነሳ ማድረግ፣

16.8 ከቀረበው የምግብ ዓይነት ውጭ የሀኪም ትዕዛዝ ካላቀረበ በስተቀር መጠየቅ፣ መጨቃጨቅ፣ መጣላት

16.9 ያለ ፈቃድ ምግብ ከተማሪዎች ምግብ ቤት ማስወጣት ወይም ለማስወጣት መሞከር

16.10 በዩኒቨርሲቲው ግቢዎች አጥር ዕቃ ማውጣት ወይም መቀባበል

16.11 ሀሰተኛ መረጃ ማሰራጨት

16.12 ማንነትን ለመለየት አዳጋች የሚያደርጉ አለባበሶችን መልበስ አይፈቀድም::

16.13 የተተለተለ፣ የተቀደደ፣ ገላን የሚያሳይ ልብስ መልበስና ጸጉርን ማንጨብረር፣ ቅርጽ ያለውና የተለየ ቀለም መቀባት፣

16.14 ፀጥታን የሚያደፈርሱ ወይም የሰዎችን ትኩረት የሚረብሹ ከፍ ያለ ድምጽ የሚያወጡ ጫማዎችን መጫማት

17. ለአንድ ወሰነ ትምህርት /አንድ ሴሚስተር/ ከትምህርት የሚያሳግዱ ጥፋቶች፣

17.1 ከዚህ በላይ በውስጠ ደንብ ቁጥር 16 ከተጠቀሱት አንደኛውን የሥነ ስርዓት ጥሰት ተፈፅሞ በተወሰደው ቅጣት ሳይሻሻሉ ያንኑ ወይም ተመሳሳይ የሥነ ስርዓት ጥሰት መፈጸም፤

17.2 በዩኒቨርሲቲው ውስጥ የሚካሄድ አካዳሚያዊ፣ አስተዳደራዊ፣ ማህበራዊ፣ ስፖርታዊ ወይም ሌሎች እንቅስቃሴዎችን መረበሽ ወይም ተገቢ ያልሆነ ጣልቃ ገብነት መፈጸም፤

17.3 የተለጠፉ ሕጋዊ ማስታወቂያዎችን ማንሳት፤



በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
Federal Democratic Republic of Ethiopia Addis Ababa University

17.4 በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ጸብ መፍጠር፣ አምባ ጓሮ መፍጠርና ሰላም ማደፍረስ

17.5 ጫትንና ሌሎች ሱስ አስያዥ በመሆናቸው የተከለከሉ ነገሮችን በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ይዞ መገኘት፣ መጠቀም፣ ወደ ዩኒቨርሲቲው ማስገባት ወይም ለማስገባት መሞከር፣

17.6 የዩኒቨርሲቲው ተማሪ ያልሆነ ግለሰብ በመኝታ ክፍል ውስጥ ማስተናገድ፣ ማስተኛት፤

17.7 የዩኒቨርሲቲው ንብረት ከሆኑ መጻሕፍት ገፆችን መቅደድ ወይም መገንጠል፤

**18. ለአንድ ወሰን ትምህርት /አንድ ሴሚስተር/ የትምህርት ማስረጃ የሚያስይዙ ጥፋቶች፣**

ዕጩ ምሩቃን በዚህ ውስጠ ደንብ ቁጥር 17 ላይ የተዘረዘሩትን ጥፋቶች ፈፅመው ሲገኙ

**19. ለአንድ የትምህርት ዓመት ከትምህርት የሚያሳግዱ ጥፋቶች፣**

19.1 ከዚህ በላይ በዚህ ውስጠ ደንብ ቁጥር 17 ከተጠቀሱት አንደኛውን የሥነ ሥርዓት ጥሰት ፈፅሞ በተወሰደው ቅጣት መሻሻል ሳያሳይ ለሁለተኛ ጊዜ ያንኑ ወይም ተመሳሳይ የሥነ ሥርዓት ጥሰት ተፈፅሞ ሲገኝ፤

19.2 ፈተና መኮረጅ፣ ማስኮረጅ ወይም ለመኮረጅም ሆነ ለማስኮረጅ ሙከራ ማድረግ፤

19.3 አንድን ግለሰብ መሳደብ፣ ክብርን ማውረድ፤

19.4 በቃል ወይም በጽሑፍ ወይም በኤሌክትሮኒክ ወይም በሌላ የመገናኛ መንገድ የኃይል፣ የጥላቻ፣ የዛቻ፣ አጸያፊ ወይም ከመልካም ጸባይ ተቃራኒ የሆነ ወይም የሌላውን ሃይማኖት፣ ብሔር፣ አስተሳሰብ፣ ማንነት ማንቋሸሽ ወይም መሳደብ ወይም ይህንኑ መልዕክት ለማንኛውም የዩኒቨርሲቲው ማኅበረሰብ አባል ማስተላለፍ፤

19.5 አጸያፊ፣ አሸባሪ፣ ሕገ ወጥ ወይም አስደንጋጭ ፖስተሮችን፣ ማስታወቂያዎችን፣ ምልክቶችን ወይም ሌሎች ነገሮች መለጠፍ ወይም ማሰራጨት፣

19.6 አጥር ዘሎ መግባት ወይም መውጣት፤ መታወቂያን ለሌላ ሰው አሳልፎ መስጠት፣ ያልተፈቀደ መታወቂያ ይዞ መገኘት፣ በሌላ ሰው መታወቂያ መጠቀም፣ በአጥር እቃ መቀባበል፣

19.7 አደንዛዥ ዕጽ ወይም አልኮል መጠጦችን በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ይዞ መገኘት፣ መጠቀም፣ ወይም ወደ ዩኒቨርሲቲው ማስገባት ወይም ለማስገባት መሞከር፤

19.8 ሳይፈቀድ በዩኒቨርሲቲው በይነመረብ (ኔትወርክ) ውስጥ መግባት ወይም ለመግባት ሙከራ ማድረግ፤

19.9 ተማሪ፣ ሠራተኛ፣ መምህር ወይም ወደዩኒቨርሲቲው የተጋበዘ እንግዳ ሥራውን እንዳያከናውን ወይም ኃላፊነቱን እንዳይወጣ ማደናቀፍ፣ መረበሽ ወይም ጣልቃ መግባት፤

19.10 ተማሪን፣ ሌላ የዩኒቨርሲቲው ማኅበረሰብ አባልን ወይም የዩኒቨርሲቲውን እንግዳ ማስፈራራት፣ ማስጨነቅ፣ መሳደብ፣ በኃይለ ቃል ወይም በዛቻ ሰላም መንሳት፤

19.11 ማንኛውንም አይነት የጾታ ትንኮሳ ወይም ጥቃት መፈጸም፤



የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
Federal Democratic Republic of Ethiopia Addis Ababa University

19.12 አደገኛ ወይም ጎጂ ኬሚካሎችን ይዞ መገኘት፤

19.13 ተቃራኒ ጾታን ወደ መኝታ ቤት ማስገባት፣

**20. ለአንድ ዓመት የትምህርት ማስረጃ የሚያስይዙ ጥፋቶች፣**

ዕጩ ምሩቃን ከዚህ በላይ በዚህ ውስጠ ደንብ ተራ ቁጥር 19 ላይ የተዘረዘሩትን ጥፋቶች ፈፅመው ሲገኙ፤

**21. ለሁለት የትምህርት ዓመት ከትምህርት መርሃ ግብር የሚያሳግዱ ጥፋቶች፣**

21.1 ከዚህ በላይ በዚህ ውስጠ ደንብ ቁጥር 19 ከተጠቀሱት አንደኛውን የሥነ ሥርዓት ጥሰት ፈፅሞ በተወሰደው ቅጣት መሻሻል ሳያሳይ ለሁለተኛ ጊዜ ያንኑ ወይም ተመሳሳይ የሥነ ሥርዓት ጥሰት ፈፅሞ ሲገኝ፤

21.2 በፈተና ወይም ምርምር ላይ የማጭበርበር ተግባር መፈጸም ወይም ለዚህ ተባባሪ መሆን፤ ማታለል ወይም የማጭበርበር ድርጊት መፈጸም ወይም ሀሰተኛ ማረጋገጫ ወይም ሰነድ ማቅረብ፣ መስጠት፤

21.3 ለሌላ ሰው መፈተን ወይም ሌላ ሰው ማስፈተን፤

21.4 በዩኒቨርሲቲው መገልገያ መሣሪያዎች ወይም ማኅበረሰብ ላይ ጉዳት ማድረስ ወይም ደህንነታቸውን አደጋ ላይ መጣል፣ ዋጋ ማሳጣት

21.5 ስርቆት፣ ዘረፋ ወይም ቅሚያ መፈጸም ወይም እነዚህን ለመፈጸም መሞከር፤

21.6 ማንኛውም የጦር መሳሪያ፣ ፈንጂ፣ ጩቤ ወይም ተመሳሳይ መሳሪያ ወደ ዩኒቨርሲቲው ማስገባት፣ ወይም ለማስገባት መሞከር፤ ይዞ መገኘት፤

21.7 የኃይል ጥቃት መፈጸም ወይም መደባደብ፤

21.8 በዩኒቨርሲቲው ቅጥር ግቢ ውስጥ የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈፀም፤

**22. ለሁለት ዓመት የትምህርት ማስረጃ የሚያስይዙ ጥፋቶች፣**

ዕጩ ምሩቃን ከዚህ በላይ በዚህ ውስጠ ደንብ ቁጥር 21 ላይ የተዘረዘሩትን ጥፋቶች ፈፅመው ሲገኙ፤

**23. ከዩኒቨርሲቲ የትምህርት መርሃ ግብር መሰናበትን/መባረርን የሚያስከትሉ ጥፋቶች**

23.1 ከዚህ በላይ በዚህ ውስጠ ደንብ ቁጥር 21 ከተጠቀሱት አንደኛውን የሥነ ሥርዓት ጥሰት ፈፅሞ በተወሰደው ቅጣት መሻሻል ሳያሳይ ለሁለተኛ ጊዜ ያንኑ ወይም ተመሳሳይ የሥነ ስርዓት ጥሰት ፈፅሞ ሲገኝ፣

23.2 በተጭብረበረ የትምህርት ማስረጃ እና ተመሳሳይ መረጃ ተመዝግቦ መገኘት፣

23.3 በዩኒቨርሲቲው ቅጥር ግቢ ውስጥ የአካል ጉዳት ወይም ሞት ሊያስከትል የሚችሉ ስለታማና ተተኳሽ መሳርያዎችን ወይም መርዛማ ነገሮችን ይዞ መገኘት፣ ለማስገባት መሞከር፣



Federal Democratic Re... Addis Ababa Univ...

23.4 ተማሪው ባገኘው ውጤት ቅር በመሰኘት በመምህሩ ወይም በቤተሰቡ ላይ ጉዳት ለማድረስ መሞከር ወይም ማድረስ፣

23.5 ድምፅ ባለው ወይም በሌለው መሣሪያ የዩኒቨርሲቲ ማኅበረሰብ አባል፣ ወይም እንግዳ መጉዳት ወይም ለመጉዳት መሞከር፣

23.6 አስገድዶ መድፈር ወይም ለመድፈር ሙከራ ማድረግ፣

23.7 በመመገቢያ አዳራሾች ውስጥና አካባቢ ከምግብ ጋር ተያይዞ በየትኛውም ምክንያት ዓመጽ፣ አድማ ማስነሳት ወይም ለማስነሳት መሞከር፣ በስራ ላይ ያሉትን ሠራተኞች መደብደብና ማስፈራራት፤

## ክፍል ሰባት
## የቅጣት አወሳሰን

**24. የቅጣት አወሳሰን**

24.1 ቅጣት የሚወሰነው የጥፋቱ ክብደት እና የተማሪው የግል ሁኔታ ግምት ውስጥ ገብቶ ለማስተማር፣ ለማረም ወይም ጥፋቱ እንዳይደገም ለማድረግ ነው፡፡

24.2 ጥፋት መፈጸሙ በተረጋገጠበት ተማሪ ላይ የሚጣለው ቅጣት ክብደት፣ የጥፋቱ ዓይነት፣ የደረሰው ጉዳት መጠን፣ በተበዳይ ላይ የደረሰው ጉዳት፣ ጥፋቱ በዩኒቨርሲቲው ማኅበረሰብ ላይ ያስከተለው ውጤት እና መሰል ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ ገብተው የሚወሰን ይሆናል፡፡

24.3 ቅጣቱ ከተፈጸመው ጥፋት ጋር ተመጣጣኝ መሆን አለበት፡፡

24.4 የሚጣለው ቅጣት በቅጣትነት ከተዘረዘሩት አንዱን ወይም እንደአግባቡ በጣምራ ሊወሰን ይችላል፡፡

24.5 ለአንድ ጥፋት ከአንድ ጊዜ በላይ ቅጣት አይጣልም፡፡

24.6 አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ቅጣቱ በማስታወቂያ ሰሌዳ እንዲለጠፍ ወይም የዩኒቨርሲቲው ማኅበረሰብ እንዲያውቀው ሊታዘዝ ወይም ሊደረግ ይችላል፡፡

24.7 ተቋማዊ ጥፋት ሲፈጸም የተማሪዎች ዲን፣ የትምህርት ክፍሉ ወይም አገልግሎት ሰጪው ክፍል ጉዳዩን ለዲሲፕሊን ኮሚቴ ማቅረብ ሳያስፈልገው የቃል ማስጠንቀቂያ ወይም የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት ይችላል፡፡ አካዳሚክ ጥፋት ሲፈጸም በአካዳሚክ ክፍሉ ቅጣቱ ሊጣል ይችላል፡፡ የተወሰደው እርምጃ የተማሪው ሪከርድ አካል መደረግ አለበት፡፡

24.8 በዚህ ውስጠ ደንብ የሚወሰን ቅጣት፣ ጥፋተኛ የተባለውን ተማሪ ያደረሰውን ጉዳት ከመካስ ወይም በሌላ ሕግ ያለበትን ተጠያቂነት አያስቀርም፡፡

25. **የቅጣት ማክበጃ**

25.1 ተማሪው ከዚህ በፊት በሌላ የዲሲፕሊን ጥፋት ተከሶ የተቀጣ ወይም በቃል ማስጠንቀቂያ የታለፈ ከሆነ፤ ወይም

25.2 ጥፋተኛው ድርጊቱን በድጋሚ ወይም በተደጋጋሚ የፈጸመ ከሆነ፤ ወይም

25.3 የሞራል ወይም የአካል ጉዳት የደረሰበት ግለሰብ ካለ፤ወይም

25.4 በጥፋቱ ምክንያት የደረሰ ጉዳት ካልተካሰ

26. **የቅጣት ማቅለያ**

26.1 የተማሪው የቀድሞ ባሕርይ መልካም ከሆነ፣

26.2 ተማሪው በፈጸመው ጥፋት የመጸጸት ስሜትና ድርጊት ካሳየ፤

26.3 በጥፋቱ ምክንያት የደረሰውን ጉዳት ከካሰ፣

27. **የቅጣት አፈጻጸም**

27.1 በተማሪ ላይ የሚወሰነውን ቅጣት የተማሪዎች ዲን ወይም የኮሌጅ ኃላፊ ጽ/ቤት ተከታትሎ ያስፈጽማል፡፡ የዲሲፕሊን እርምጃ የተወሰደበትን ተማሪ ተገቢው ክትትልና የካውንስሊንግ አገልግሎት እንዲያገኝ ያደርጋል፡፡

27.2 ተማሪው የማኀበረሰብ አገልግሎት እንዲሰጥ ሲወሰን የአገልግሎቱን ዓይነትና የሚያስፈጽመውን ክፍል መወሰንና ትዕዛዙ እንዲደርሰው መደረግ አለበት፡፡

27.3 የሚወሰደው እርምጃ የተማሪው ሪከርድ አካል ይሆናል፡፡ የትምህርት ክፍሉና ተገቢው አካል እንዲያውቀው ይደረጋል፡፡ የተፈጸመው ጥፋት አካዳሚያዊ ከሆነ ቅጣቱ የአካዳሚ ሪከርዱ አካል ይሆናል፡፡ ሌሎች ጥፋቶች የዲሲፕሊን ሪከርድ አካል ይሆናሉ፡፡

27.4 የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ወይም ከጽሑፍ ማስጠንቀቂያ በላይ የተቀጣና የቅጣት ሪኮርዱ ያልተሰረዘለት ተማሪ ለተማሪዎች ኀብረት ምርጫ ውድድር አይቀርብም ፡፡

27.5 ተማሪው ቅጣት ከተጣለበት በኂላ እስኪመረቅ ድረስ ወይም የቃል ማስጠንቀቂያ ከሆነ፣ ለስድስት ወራት፣ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ከሆነ ለዘጠኝ ወራት፣ ከጽሑፍ ማስጠንቀቂያ በላይ ከሆነ ለሁለት ዓመት ተመዝግቦለት ከቆየ በኂላ መልካም ባሕርይ ካሳየ በሪኮርዱ ውስጥ የተያዘው ጥፋት ይሰረዝለታል፡፡

## ክፍል ስምንት
## የዲሲፕሊን እርምጃ አወሳሰድና ውሳኔ ሰጪ አካላት

28. መርህ

28.1 የሥነ ሥርዓት ጥሰት እና የእርምት እርምጃ በሚወሰድበት ጊዜ ተማሪዎች በተመሳሳይ ሁኔታ መስተናገድና በእኩልነት የመታየት መብት አላቸው።

28.2 ቀላል የዲሲፕሊን ቅጣት ከሚያስከትሉ ጉዳዮች ውጭ የሥነ ሥርዓት ጥሰት ፈጽሟል ተብሎ ክስ የቀረበበት ተማሪ የቀረበበትን ክስ የማወቅ፣ ራሱን የመከላከል እና የመሰማት መብት አለው።

28.3 የሥነ ሥርዓት ጥሰት መፈጸሙ ከተረጋገጠ ከጥፋቱ ጋር ተመጣጣኝ ቅጣት መጣል አለበት።

29. ጊዜያዊ እርምጃ

29.1 ማንኛውም መምህር ወይም የአገልግሎት ሰጪ ተቋም ኃላፊ የሥነ ምግባር ደንቡን በመጣስ በመማሪያ ክፍል፣ ላብራቶሪ፣ ወይም አንድ ኩነት በሚካሄድበት ጊዜ የዩኒቨርሲቲው ክፍል ተገቢ ያልሆነ ባሕርይ ያሳየ ወይም የረበሸ ተማሪ ለዕለቱ እንዲወጣ ማድረግ ይችላል። ለጥፋቱ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ለተገቢው አካል ያሳውቃል።

29.2 የተማሪዎች ዲን ከጉዳዩ አጣዳፊነት አንጻር ወይም ተጨማሪ ጉዳት እንዳይደርስ ወይም ተጨማሪ የሞራል ጉዳት እንዳይደርስ ወይም ዩኒቨርሲቲውን ወይም የዩኒቨርሲቲውን ማኀበረሰብ አባል ጥቅም ወይም ደህንንት ለመጠበቅ ሲባል ተማሪውን ለጊዜው ማገድ ይችላል። ጊዜያዊ እገዳው በዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት ወይም ተወካዩ ካልተራዘመ በስተቀር ከአስር የሥራ ቀናት ሊበልጥ አይችልም።

30. ጥፋቶችን ማሳወቅ

30.1 ማንኛውም የዩኒቨርሲቲው ማኀበረሰብ አባል በዚህ ውስጠ ደንብ የተመለከቱት ጥፋቶች ተፈጽመው ሲያገኝ ለኮሌጅ ወይም ለትምህርት ክፍል ወይም ኢንስቲቲዩት ወይም ለተማሪዎች ዲን ወይም ለዩኒቨርሲቲው ደህንነትና ጸጥታ ጽ/ቤት ወይም ለተገቢው የሥራ ክፍል ማሳወቅ አለበት።

30.2 ጥሰቱ የደረሰበት አካል ጉዳዩን መርምሮ በቂ ማስረጃ አለ ብሎ ካመነ አቤቱታ ያቀርባል። ማስረጃው በቂ ካልሆነ ተጨማሪ ምርመራ እንዲደረግ ወይም ጉዳዩን ለመዝጋት ይችላል።

31. አቤቱታ ማቅረብ

31.1 ተገቢው የትምህርት ክፍል፣ የተማሪዎች ዲን ወይም የኮሌጅ ዲን፣ የት/ክፍል ኃላፊ፣ የኢንስቲቲዩት ዳይሬክተር፣ ወይም የዩኒቨርሲቲው ማኀበረሰብ አባል የሆነ ማንኛውም

ተበዳይ ሰው የሥነ ሥርዓት ጥሰት በፈጸመ ማንኛውም ተማሪ ላይ አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፡፡

31.2 አቤቱታው በጽሑፍ ሆኖ ፍሬ ነገሩን በአጭሩ በበቂ ሁኔታ መግለጽና ማስረጃዎችን ማመልከት አለበት፡፡

31.3 አቤቱታውን ከተገቢው መረጃና ማስረጃ ማጣራት ጋር ለተማሪዎች ዲን ወይም ለኮሌጅ ዲን በግቢ ጸጥታ ጽ/ቤት በኩል ያቀርባል፡፡ አቤቱታው መቅረብ ያለበት ድርጊቱ በተፈጸመ ወይም መፈጸሙ በታወቀ ከአስር የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ነው፡፡

31.4 አቤቱታው በሁለት ቅጂ ተዘጋጅቶ በተማሪዎች ዲን ወይም በኮሌጅ ዲን በኩል ከሶስት የሥራ ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለተማሪዎች ዲሲፕሊን ኮሚቴ ይቀርባል፡፡

31.5 አቤቱታው እንደቀረበ ሁሉም ሂደቶች እና ውሳኔዎች የሚመዘገቡበት ፋይል ተከፍቶ ለኮሚቴው ይቀርባል፡፡

## 32. ምርመራ

አቤቱታ የቀረበለት የተማሪዎች ዲሲፕሊን ኮሚቴ የቀረበው አቤቱታ በቂ ስለመሆኑ መርምሮ ውድቅ ሊያደርገው ወይም እንዲሰማ ሊወስን ወይም በአቤቱታ አቅራቢና በተከሳሽ ስምምነት በአስተዳደራዊ መንገድ እንዲያልቅ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## 33. አቤቱታ መስማትና ምርመራ

32.1 ኮሚቴው በቀነ ቀጠሮ ግራ ቀኙን አስቀርቦ ግልጽ ባልሆኑ ጉዳዮች ላይ ማጣራት ያደርጋል፡፡ የአንዱ ወገን አለመቅረብ የጉዳዩን መሰማት አይከለክልም፡፡

32.2 እያንዳንዱ ተከራካሪ ወገን ጉዳዩን የማስረዳት ኃላፊነት አለበት፡፡ ሆኖም ተማሪው አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው በአማካሪ ሊረዳ ይችላል፡፡ የትርጉም አገልግሎት የሚፈልግ ተማሪ ከአስተርጓሚ ጋር ሊቀርብ ይችላል፡፡ ባለጉዳዩ አማካሪው ወይም አስተርጓሚ ካጣ ዩኒቨርሲቲው አንድ ሰው ሊመድብለት ይችላል፡፡

32.3 ኮሚቴው በግራ ቀኙ የቀረቡትን ማስረጃዎች ይሰማል፤ ይመረምራል፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ከየትኛውም የዩኒቨርሲቲው አካል ማስረጃዎች እንዲቀርቡለት ወይም ምስክሮች ቀርበው እንዲሰሙ ማድረግ ይችላል፡፡

32.4 ምስክሮች ሲሰሙ ለምስክሮች ጥያቄ የሚያቀርበው ኮሚቴው ይሆናል፡፡ ተከራካሪ ወገኖች የሚቀርብ ጥያቄ ካላቸው ለኮሚቴው ማሳወቅ ይችላሉ፡፡

32.5 በአንድ አቤቱታ ከአንድ በላይ ተማሪዎች ከተከሰሱ ኮሚቴው ጉዳዩን አጣምሮ ወይም በተናጠል እንዲሰማ ሊወስን ይችላል፡፡

## 34. የውሳኔ ሐሳብ

34.1 ኮሚቴው የውሳኔ ሐሳቡን ከአንድ ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ መስጠት አለበት፡፡

34.2 የውሳኔው ሐሳብ በጽሑፍ ሆኖ ለተማሪዎች ዲን ወይም ለኮሌጅ ዲን መቅረብ አለበት፡፡

34.3 ውሳኔው በማስረጃ ሚዛን ላይ ተመስርቶ የበለጠ አሳማኝ የሆነውን ወገን በመምረጥ ለዚህም ምክንያቱን በመግለጽ ይሰጣል፡፡

34.4 ውሳኔው በሙሉ ድምጽ ካልተሰጠ የአብላጫው ድምጽ ውሳኔ የኮሚቴው ውሳኔ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

34.5 የሐሳብ ልዩነት ያለው የኮሚቴው አባል ልዩነቱን በውሳኔው ላይ ማካተት አለበት፡፡

## 35. ውሳኔ

የተማሪዎች ዲን ወይም የኮሌጅ ዲን የቀረበለትን የውሳኔ ሀሳብ

35.1 የውሳኔው ሐሳብ በደረሰው ከአንድ ሳምንት ባልበለጠ ጊዜ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

35.2 ውሳኔው በጽሑፍ ሆኖ ለተከራካሪ ወገኖች ይሰጣል፡፡

35.3 የኮሚቴውን የውሳኔ ሐሳብ ሙሉ ለሙሉ የማጽደቅ፣ የማሻሻል እና ኮሚቴው እንደገና እንዲመረምር የማዘዝ ሥልጣን አለው፤

## 36. የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት /ይግባኝ

36.1 በተሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን ይግባኙን በጽሑፍ ለዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ወይም ፕሬዚዳንቱ ለወከለው/ለሚወክለው ማቅረብ ይችላል፡፡ አዲስ የክስ ጭብጥ በይግባኝ ላይ አይቀርብም፡፡

36.2 ይግባኙ መቅረብ ያለበት ውሳኔው በተሰጠ ከአስራ አምስት የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ነው፡፡

36.3 ፕሬዚዳንቱ በጉዳዩ ላይ በራሱ ውሳኔ ለመስጠት ወይም እንደውስብስብነቱ እና ከሚኖረው አንድምታ አንጻር ጊዜያዊ ኮሚቴ እንዲያየው ሊመራ ይችላል፡፡ ኮሚቴው የሚያቀርበው የውሳኔ ሐሳብ በፕሬዝዳንቱ መጽደቅ አለበት፡፡

36.4 ፕሬዚዳንቱ ውሳኔውን ለማጽናት፣ ለማሻሻል፣ ለመሻር ወይም ለተጨማሪ ምርመራ ወደ ዲስፕሊን ኮሚቴው መመለስ ይችላል፡፡ የተሰጠውን ውሳኔ በማጽናት፣ በማሻሻል ወይም በመሻር የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

## ክፍል ዘጠኝ
## የዲሲፕሊን ኮሚቴ

**37. የኮሚቴው አወቃቀር**

37.1 የተማሪዎች ዲን ወይም የኮሌጅ ዲን ቋሚ የተማሪዎች አካታችነትን ባማከለ መልኩ የዲሲፕሊን ኮሚቴ እንዲቋቋም ያደርጋል። የሚመለከተው ኮሌጅ ወይም የተማሪዎች ዲን የመሰብሰቢያ ቦታ ማዘጋጀትን ጨምሮ ለኮሚቴው ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል።

37.2 በአንድ የዩኒቨርሲቲ ግቢ ውስጥ አንድ ቋሚ የተማሪዎች ዲሲፕሊን ኮሚቴ እንዲቋቋም ይደረጋል። ይህ ኮሚቴ ባለበት ግቢ ውስጥ ለሚፈጠሩ የዲሲፕሊን ጉዳዩች ብቻ ኃላፊነት ይኖረዋል።

37.3 በዋናው ግቢ ውስጥ የሚቋቋመው የተማሪዎች ዲሲፕሊን ኮሚቴ እንደአስፈላጊነቱ በሌሎች ካምፓሶች ውስጥ የሚፈጠሩትን የዲሲፕሊን ጉዳዩች ሊያይ ይችላል።

37.4 እያንዳንዱ ኮሚቴ አምስት አባላት ይኖሩታል። የአባላቱ ውክልና እንደሚከተለው ይሆናል፡-

1) ከመምህራን አንድ ተወካይ
2) ከተማሪዎች ዲን /ከኮሌጅ ዲን ጽ/ቤት አንድ ተወካይ
3) ከተማሪ ኅብረት አንድ
4) ከተማሪዎች አገልግሎት ጽ/ቤት አንድ ተወካይ
5) ከጥበቃ ክፍል አንድ ተወካይ

37.5 የመምህራን ተወካይ በሚመለከተው ኮሌጅ ወይም የተማሪዎች ዲን የሚሰየም ይሆናል።

37.6 የኮሚቴው አባላት ሥራቸውን ሲያከናውኑ ለሕሊናቸውና ለሕግ ብቻ ተገገር ይሆናሉ።

**38. የኮሚቴው አባላት አሰያየም**

38.1 የኮሚቴው አባላት የሚመረጡት በሚከተለው መስፈርት ነው።

1) በመልካም ሥነ ምግባር የሚታወቅ
2) በሥነ ምግባር ጉድለት ተቀጥቶ የማያውቅ
3) በዩኒቨርሲቲው ቢያንስ አንድ ዓመት አገልግሎት ወይም ቆይታ ያለው
4) አገልግሎቱን በፍትሐዊነት ለመስጠት የሚያስችል ብቃትና ባሕርይ ያለው

**39. የኮሚቴው ስልጣን**

ኮሚቴው በቀረበለት የዲሲፕሊን ጉዳይ ላይ የውሳኔ ሐሳብ ያቀርባል።

**40. የኮሚቴው አሰራር**

40.1 ኮሚቴው ከአባላቱ መካከል በተማሪዎች ዲን ወይም በኮሌጅ ዲን የሚሰየም አንድ ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢ እና ጸሐፊ ይኖረዋል።

40.2 ሰብሳቢው የኮሚቴውን ስብሰባ በሊቀመንበርነት ይመራል፡፡ ሰብሳቢው በማይኖርበት ጊዜ ምክትሉ ኃላፊነቱን ይረከባል፡፡

40.3 ጸሐፊው የኮሚቴውን ቃለ ጉባኤ ይይዛል፡፡

40.4 አብላጫው የኮሚቴ አባላት ከተገኙ ስብሰባውን ማካሄድ ይቻላል፡፡

### 41. የአባላት መጓደል

የኮሚቴው አባላት የተጓደሉ ከሆነ የተማሪዎች ዲን ወይም የኮሌጅ ዲን በተመሳሳይ ሁኔታ ተተኪ ይመድባል ወይም እንዲመደብ ያደርጋል፡፡

### 42. የአባላት መነሳት

የሚታየው ጉዳይ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የኮሚቴ አባል የሆነውን ሰው የሚመለከት ከሆነ ወይም የፍላጎት መጋጨትን በመፍጠር ተገቢውን ዳኝነት ለመስጠት የማያስችል ሁኔታ ሲኖር የኮሚቴው አባል ይህን ጉዳይ በተመለከተ ከአባልነት እንዲነሳ ይደረጋል፡፡

## ክፍል አስር
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 43. ተባባሪ ስለመሆን

በዚህ ውስጥ ደንብና በሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች የተከለከሉ ድርጊቶችን ከሚፈጽም ማንኛውም አካል ጋር ተባባሪ እና ድጋፍ ሲሰጥ የተገኘ ተማሪ ራሱ የዲሲፕሊን ግድፈት እንደፈፀመ ተቆጥሮ ከዋናው ድርጊት ፈፃሚ እኩል ይቀጣል፡፡

### 44. የተጠያቂነት ገደብ

ተማሪዎች መብታቸውን ለማስከበር በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ወይም ሂደት በማንም ወይም በምንም ነገር ላይ ጉዳት እስካላደረሰ ድረስ ወይም በቅን ልቦና በሚያከናውኑት ተግባር ወይም በአጋጣሚ አደጋ ለሚከሰት ነገር ወይም በልዩ ሁኔታ በሚፈቀድበት ሁኔታ ለሚፈጸም ተግባር ወይም ጥፋት አይጠየቁም፡፡

### 45. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች

ከዚህ በፊት ሲሠራበት የነበረው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የተማሪዎች ሥነ ሥርዓት ደንብ ቁጥር 1/2011 በዚህ የዲሲፕሊን ውስጥ ደንብ የተተካ ስለሆነ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡ የተማሪዎች ዲሲፕሊንን የሚመለከቱ ሌሎች ሕጎችና ልማዳዊ አሠራሮች በዚህ ውስጥ ደንብ በተጠቀሱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

46. ማሳወቅ

46.1 የተማሪዎች ዲን ጽ/ቤት አዲስ ገቢ ተማሪዎች ትምህርት ከመጀመራቸው በፊት ይህን ውስጠ ደንብ በዝርዝር እንዲያውቁት ያደርጋል፡፡

46.2 ውስጠ ደንቡ ለአዲስ ገቢም ሆነ ለነባር ተማሪዎች በተለያየ መንገድ ተደራሽ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

47. **የመተባበር ግደታ**

ለዚህ ውስጠ ደንብ ተግባራዊነት ሁሉም የአዲስ አባባ ዩኒቨርሲቲ ማኅበረሰብ አባላት የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

48. **ውስጠ ደንብ ስለ ማሻሻል**

ይህ ውስጠ ደንብ አጥጋቢ ምክንያቶች ሲኖሩ በማንኛውም ጊዜ ሊሻሻል ይችላል፡፡

49. **ውስጠ ደንቡ ስለሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ውስጠ ደንብ በሴኔት ሕጉ አንቀጽ 148(3)(1) መሠረት የወጣ ሲሆን የአዲስ አባባ ዩኒቨርሲቲ ሴኔት ካጸደቀበት ጥቅምት 12 ቀን 2017 ዓ. ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡